# “ለዚህ ያደረሰን እግዚአብሄር ይመስገን”



-በኦስሎ የኢ.ኦ. የቅ/ገብርዔልና ያቡነ ተ/ሃይማኖት ቤ/ክ. ምእመናን መሪ መዝሙር

“መስክሩ... ድንቅ ሥራን መስክሩ
ለዓለም ሁሉ ንገሩ” መጽሃፉ እንዲል፣ እኛም ያየነውን ሁሉ በእውነት ስለእውነት እንዲህ እንመሰክር ዘንድ አዶናይ አዘዘነ... ተቤጀነ።

በኦስሎ የኢ.ኦ. የቅ/ገብርዔልና ያቡነ ተ/ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አንድ አዲስ የእድገት ምእራፍን ከትናንት በስቲያ በዋለው እለተ ቀዳሚት አስመዝግባለች። ጥር 8 ቀን 2002 ዓ.ም. ተብሎ በሚጠቀሰው በዚህ እለት አዲስ የቤተክርስቲያን ሕንጻን ተረክባ፤ መንበረ ታቦቱን አስከብራለች። ለሦስት ሰዓታት በላይ በፈጀው በዚህ ታላቅና ደማቅ መንበረ ታቦቱን የማስከበር ሥነ ሥርዓት ላይ፣ በኦስሎና አካባቢዋ የሚኖሩ የቤተክርስቲያኒቷ ምእመናን ተገኝተዋል።



ቆሞስ መልአከ ጽዮን አባ አብርሃም ገብረ ሚካዔል የደብሩ አስተዳዳሪ በሥነ ሥርዓቱ ላይ ለተገኙት ምእመናን በሰጡት አባታዊ ቃለ በራኬ ላይ፣ የልብ ውስጠኛውን ስሜታቸውን አልሸሸጉም። ከሁለቱ ጸላቶች ጋር በደባልነት ከሦስት ዓመታት ተኩል በላይ ሲኖሩ፣ አምላክን በእምባቸው እያጣቀሱ ደጋግመው ሠራዬ መፍትሄን ይሰጣቸው ዘንድ ተማጽነውታል። “ሰው ነኝ። እናም ከጽላት ጋር አብሮ በደባልነት የመኖር ብቃት የለኝም። ከፋና በጎ ከሰው ጋር መነጋገር አለ... ቲቪ ማየት አለ.. (ወዘተ... ወዘተ...) እናም አንድ ቤተክርስቲያን አግኝተን



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

መንበረ ታቦቱን እናስከብር ዘንድ አምላክን አጥብቄ እለምን ነበር" ሲሉ እምባቸውን እያበሱ ትሁት የልብ ሃሳባቸውን ገልጸዋል። ያን ልመናቸውንና እግዚኦታቸውን አምላክ ሰማ። የደጋግ ምእመናኑንም ካንድ አሥርት በላይ የዘለቀ የራስ ቤተክርስቲያንና ቤተመቅደስ ጥያቄ ልዑል እግዚአብሄር መለሰ። ድንቅና ቅጹብ ሥራን ሠራ... አምላክ። ግሩም የቤተክርስቲያን ሕንጻን ሰበካ ጉቤዔው ተረክቦ እነሆኝ አለ ለምእመኑ። ምእመኑም በዚያ አዲስ አምባ ተሰባስቦ የታቦቱን መክበር ሥርዓትና ኡደት "ግሩም ድንቅ ያንተ ሥራ..." እያለ እየዘመረ አብሮ ሲያከብር አመሸ። "ተመስገን ነው... ለሱ ምን ይሳነዋል!" ሲሉም ብዙዎች ተደምጠዋል።

የዚህ ዜና መዋእል አቅራቢ የዛሬ ሁለት አመታት አካባቢ ቤተክርስቲያኒቱ ያዘጋጀችውን አውሮፓ አቀፍ መንፈሳዊ ጉባዔ አስመልክቶ ዘግቦት በነበረ ዜና ላይ እንዲህ ሲል አንድ የማትጊያ መልእክት አስተላልፎ እንደነበር ትዝ ይለዋል። እንዲህ ይጠቀሳል ተዚያ ዜና መዋእል...



*"ይህ የበቃ የነቃ ያመራር ችሎታችሁ በነካ እጃችሁ አንዲት የመሰባሰቢያ አጸድ ያላት የቤተ ክርስቲያን ጎጆ እንቀልስ ዘንድ የሙሴን በትር እንደያዛችሁ ምሩን ልንላቸውም ይገባል። ተሰው ቤት አውጡን ለማለት ነው። እኛ ባገራችን ባምባችን ባጥቢያችን ታቦታችን ለጥምቀት ታልሆነ በቀር ተቤታችን ወጥቶ ከባእድ ቤት አድሮብን አያውቅምና፤*



*"ጎበዝ እንበርታ፥ እንረዳዳ*
*እኛ ምን አለን፥ ተሰዉ ጓዳ*
*ታቦት አይወድም ባዳ*
*ምሰሶው ይቁም፥ ይታይ ተራዳ*
*አንተው ነህ ከፋይ፥ የራስክን እዳ*
*የ'ምነትክን ጉማ፥ የምድርን ፍዳ፤*
*ጎበዝ በርታ በል፥ ገብርዔልን ይዘህ*
*ተክልዬን ምርኩዝ፥ መሰላል ተክለህ"*



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

*ድር ቢያብር አምበሳ ያስርን ደሞ ያው በቀደም አሳይታችሁናልና በሱ በጌታ ፈቃድ የማይቻል የለምና ይቺን ትንሽ ምድራዊ ግብር እንፈጽማታ! ለማንኛውም ሥራችሁን ሁሉ አምላክ በበረከቱ ይባርክ!...”* ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም.

እናም ያ ምልጃ ያ ምኞት ያ ተስፋ ቀኑን ጠብቆ ባባታችን በአባ አብርሃም መልካም አመራር፥ በሰበካ ጉባዔ አባላት ትጋትና በምእመናኑ ያላሰለሰ ጥረት ዛሬ እውን ሊሆን ችሏል። በጠላት ዲያብሎስ ላይ ድልን እንዲህ በግልጽ እንደመቀዳጀት አንድን የክርስትና እምነት ተከታይ ምእመን የሚያስደስተው አንዳችም ነገር የለምና ለታቦቱ መንበርን ማግኘቱ ታላቅ ፍጻሜ ነው።

አንድ አዲስ ቤተ ክርስቲያንና ታቦት ሲከብር ሥርዓቱን ማካሄድ የሚችለው ከቆሞስ በላይ ያለ የበቃ ካህን ብቻ ነው። በዚህ የቤተክርስቲያናችን ቀኖና መሠረት አባ አብርሃም የዚህ ማእርግና ተክህኖ ስላላቸው፤ በቆሞስነታቸው ይህን ታላቅ ሥርአት በታላቅ መንፈሳዊ ክህሎት መርተውታል። ከጸመ ድጓ፥ ከኦሪት፥ ከዳዊት መዝሙር፥ ከሃዲስና ከመሳሰሉት መጻህፍት በተውጣጣ ጸሎት ቤተክርስቲያኑ ከብሯል። አባ አብርሃም በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በጉራጌ ዞን በነበሩበት ጊዜ ከሃያ በላይ አዳዲስ ቤተክርስቲያናትን ያስከበሩ (በክህነት ቋንቋ ቤተክርስቲያን “ከበረ” እንጂ “ተመረቀ” እንደማይባል እዚህ ላይ ያጤኗል) አባት ናቸው።



እገረ መንገዳችንን አንዳንድ ጠቃሚ ጥያቄዎችን ላባ አብርሃም ማንሳታችንም አልቀረም ነበር። አባ አብርሃም ለሁሉም ወግ ያለው ምላሽ ሰጥተውል፡፡ ከምላሻቸው የጥያቄያችን ውል ምን እንደነበር መጨበጥ ያስችላልና እንሆ... “ምሁር ኢየሱስ ከሚባለው ገዳም ታቦቶቹን (የቅ/ ገብርዔልንና ያቡነ ተክለ ሃይማኖትን ) ይዤ ወደዚህ ወደ ኖርዌይ የመጣሁት እኔው



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

እራሴ ነኝ። በዞኑ ሊቀ ጳጳስ በአቡነ መልከ ጻዴቅ መልካም ችሮታና ቡራኬ እኒህ ጽላቶች ለዚህ ለኦስሎ ምእመን ቤዛነት ሊበቁ ችለዋል።” ብለዋል።

አባም በእለቱ በጸሎትና በሜሮን ጸበል የቤተክርስቲያኒቱን ሕንጻ ባርከው፤ መንበረ ታቦቱን አስከብረዋል። በዚህ ታላቅና ደማቅ ሥነ ሥርአት ላይም የቀሳውስትንና የካህናትን የተጓደለ ቁጥር ለመሙላትና ሥርአተ ጸሎቱን ምሉእ ለማድረግ እንዲያስችል የተወሰደ እርምጃ ነበር። ይሄውም አባ አብርሃም፣ ከኤርትራ እህት ቤተክርስቲያን አንድ ቄስና አንድ ዲያቆን በግል በመጋበዝ ሥርዓተ ጸሎቱን የተሟላ ለማድረግ መቻላቸው ነበር። ቀሲስ ሳሙዔልና ዲያቆን አማኑዔል እውነትም የሳሳውን የካህን ጎናችንን ደህና አድርገው በመደጎም ሥርዓቱን ውበትና ድምቀት አላብሰውት ቆይተዋል። በሌላም በኩል በሁለቱ ወንድማማች ሕዝቦች መካከል ያለውን የደምና የሥጋ ግንኙነት የሚያጸናና ሰይጣንን ፊት የሚነሳ ተግባር በመሆኑ፣ የብዙዎችን ይሁንታ ያገኘ ቅዱስ ተግባር መሆኑ በምእመናን ዘንድ ተጢኗል።

ይህንን የካህናት እጥረት ለማሟላትም በቅርቡ መንበረ ጵጵስናቸው በስዊድን የሆኑትን አባታችንን አቡነ ኤልያስን የኦስሎ ቤተክርስቲያናችን ጋብዛ፣ ለወጣት ዲያቆናት የክህነት ማእርግ እንደሚሰጡ ታውቋል። ይህም የደብሩን መንፈሳዊና ማህበራዊ አገልግሎት በብርቱ ለማጠናከር እንደሚያስችል አባ አብርሃም አስምረውበታል። ያቡነ ኤልያስ እዚህ መገኘት ለዚህ ላዲሱ ክርስቲያናዊ የቤተክርስቲያኒቱ እድገት ታላቅ አስተዋጽዖ ያደረጉ ምእመናን፣ የኮሚቴ አባላትን፥ ድርጅቶችንና አካላትን ሁሉ በምስጋና እንዲባርኩ እንደሚያስችልም አባ ጠቁመዋል።



በኦስሎ የኢ.ኦ.የቅ/ገብርዔልና ያቡነ ተ/ሃይማኖት ቤ/ክርስቲያን ሰበካ ጉባዔ አመራሩን ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ ያልተቋረጠ ትረት የማድረጉን የሥራ ፍሬም ለማየት በቅቷል። እንደ ሰበካ ጉባዔው ዋና ጸሃፊ እንደ ወንድም ተሰፋ ሚካዔል መኮንን ገለጻ ከሆነ፣ ከቤተክርስቲያኒቱ ሕንጻ ባለንበረቶች ጋር እልክ አስጨራሽ ምልልስና ውጣ ውረድ ተካሂዷል። “ጌታ አንኳኩ ይከፈትላችኋል.. እንዳለው ሁሉ እኛም በርትተን *ከሺርከሊ ፌለሰ ሮደት* . Kirkelige felles rådet ጋር ባካሄድነው ድርድርና ውይይት ይህንን የቤተክርስቲያን ሕንጻ



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

መንበረ እምነታችን ልናደርገው ችለናል።" ብሏል። የቤተክርስቲያኒቱን ሕንጻ ለአምስት ዓመታት በኮንትራት የወሰዱ ሲሆን፣ ባመት ስድሳ ሺህ የኖርዌጂያን ክሮነር ይከፈልበታል። ከዚህ ቀደም ከነበረው (የጸሎት ቤት እንጂ መንበረ ታቦት ካልከበረበት ቤት) የቤት ኪራይ ጋር ሲነጻጸር ይህ በእጅጉ ንቃሽ መሆኑን ዋና ጸሃፊው አመልክተዋል። ለወደፊቱም ሕንጻውን በቤተክርስቲያኒቱ ንብረትነት ለማጽናት ወደሚያስችሉ ሕጋዊ እንቅስቃሴዎች ለመጓዝ የሚያስችሉ ጥናቶችና ዝግጅቶች እንደሚደረጉ ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል።

የቤተክርስቲያኒቱ ሕንጻ ባንድ ጊዜ ሁለት መቶ ምእመናን ማስተናገድ የሚችሉ ሁለት ሳሎኖች ያሉት ሲሆን፣ ለሌሎች መገለገያዎች የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ ክፍሎችም በተጓዳኝ ያሉት ነው። ሰበካ ጉባዔው ሕንጻውን በተረከበ ባጭር ጊዜ ውስጥ በቁጥር ጥቂት በምግባር ግን እጅግየበዙና የከበሩ ምእመናን አስተባብሮ ያከናንወነው የእድሳት ሥራ እጅግ የሚያኮራ ነው። ቀለም ከመቀባትና አዳዲስ ውብ ምንጣፎችን ከማንጠፍ አልፈው በመላእክትና በቅዱሳን ሥእሎች ውበት አዳራሾቹን አንቆጥቁጠዋቸዋል። እውስጡ ገብተው ተጥንታዊው ባለመከዳ መቀመጫ ላይ አረፍ ብለው ጣመንን እየተወጡ፣ የልብ የልብን ታንድዬ ጋር ሲጨዋወቱ ታላቅ መንፈሳዊ ድባብ ሁለንተናን ይዋጃል.... ደስ ደስም ይላል። ተመስገን ማለትም ይከተላል... ባንድ እምነትም ሳያወላውሉ መጽናትም ሃሴት አንጓች መሆኑንም ልብ ይሏል።



የቤተክርስቲያኒቱን መጻኢ አንዳንድ ተግባራትም በአባ አብርሃም በኩል ይፋ ሆነዋል። አሁን የተገኘው ሕንጻ ለተለያዩ የቤተክርስቲያኒቱ ውጥን ሥራዎች አመቺ ስለሆነ፣ በየቀኑና በየሳምንቱ የሚከናወኑ ተግባራት መኖራቸውን ጠቁመዋል። በየእለቱ ገድለ ተክለሃይማኖት ይነበባል። ቅዳሜ ቅዳሜ የጥምቀት ሥርዓት ይካሄዳል። ለወደፊቱም ቅዳሴ በየሳምንቱ ለማካሄድ የሚያስችል የካህናትና ያንዳንድ ሁናቴዎችን መሟላት እንደሚጠብቁ አባ አክለው ለምእመናኑ አስረድተዋል። ሰበካ ጉባዔው ወደፊት በሚያወጣው የስልጠናና የትምህርት መርሃ ግብር መሠረትም፤ የሃይማኖተ አበው ትምህርትና የሥነ ጽሁፍ ሥልጠና እንደሚካሄድም ለማወቅ ተችሏል።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com



እለተ ቀዳሚትን በእንዲህ ዓይነት ደማቅ ታቦትን የማስከበር መንፈሳዊ ሥርዐት ሲረካ የዋለው ምእመን፤ እለተ እሁድንም ዓመታዊ የህይማኖት በዓልን ባዲሱ የቤተክርስቲያኒቱ ህንጻ ውስጥ በማክበር ደግሞታል። አዎን... የጥምቀት በአል ታስቦ ሳይሆን ተከብሮ ውሏል ማለት ይቀላል። ከኖርዌይ ያየርና ያኗኗር ጸባይ አኳያ የጥምቀት በዓልን በእለቱ ማካሄድ ባይቻልም፤ ይቺ የኦስሎዋ ቤተክርስቲያናችን አቅምና ሁኔታ በፈቀደው ሁሉ ተጠቅማ ጥምቀትን አክብራለች። “ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ...” ብቻም ሳይሆን፤ ፍስሃና ደስታ ለመቼ ሊሆን እየተባለ ሲወረብ፥ ሲሸበሸብ ተውሏል። ጽናጽሉ፥ መቋሚያው፥ ከበሮው፥ ቃጭሉ፥ የቤተክርስቲያን ዣንጥላው ሁላ.... ለጥምቀት ሰጥ ለጥ ብሎ ሲገብርና ሲገዛ ተስተውሏል፥ ተደምጧልም። ሃጫ በረዶ የመሳሰለው ነጫጭ አልባሳትና ልብሰ ተክህኖ ሁላ ተመሽገበት ቁምሳጥን እየወጣ ጥምቀትን ጥመቀት አስመስሎት ውሏል። የቅዱስ ገብርዔልም ታቦት ሦስት ጊዜ ዑደት ካደረገ በኋላ ተመንበረ ክብሩ ተከብሯል። ተመስገን ነው!...

ከፊል የክብረቱን እንቅስቃሴ ወንድም ተስፋዬ ፍጹምና ወንድም ግርማቸው የወንድወሰን ከቀረጹልን ምስሎች ላይ ማስተዋል የሚቻል ነው።

+ወስብሃት ለእግዚአብሄር
+በአበራ ለማ (ኦስሎ፥ ጥር 10 ቀን 2002 ዓ.ም.)



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com